MCPS ROCKVILLE, MARYLAND

# 3ኛ ክፍለጊዜ የ1ኛ ክፍል ውጤት የወላጆች መመሪያ

በማርከ መስጫ 3 ወቅት፣ የ1ኛ ክፍል ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለጸው ፅንሰሀሳቦችና ክህሎቶች ትምህርት ይቀበላሉ።
እባክዎ ልብ ይበሉ፦ በ በኢታሊክስ የታዩት ጽንሰሃሳቦች እና ክህሎቶች ትምህርት ተሰጥቶባቸዋል ነገር ግን በሪፖርት ካርዱ ላይ ደረጃ/ዉጤት አልተገለጸም።

## ሒሳብ

### መለካት እና የተመዘገበ መረጃ

- ሦስት ቁሶችን በቁመት/ርዝመት ማስቀመጥ፤ በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ ሦስተኛዉን መለኪያ በመጠቀም የሁለቱን ቁሳቁሶች ቁመት/ርዝመት አወዳድር/ሪ።
- የአንድን እቃ/ቁስ ርዝመት እንደ የርዝመት አሃዶች ሙሉ ቁጥር ግለጽ/ጪ
  - በርካታ አጫጭር እቃዎችን ቅጅ (የርዝመት መለኪያ) ከጫፍ እስከ ጫፍ በማጋደም፣
  - የእቃ ርዝመት ልኬት ምንም ክፍተት ሳይኖር ወይም መደራረብ/መታጠፍ ሳይኖር ከተዘረጋዉ ተመሣሣይ የመጠን ርዝመት አሃዱዎች ቁጥር ጋር እኩል መሆኑን መረዳት፤
  - እንደሚለካው እቃ ርዝመት ሁኔታ ምንም ክፍተት ወይም መደራረብ ሳይኖር በሙሉ ቁጥር መለኪያ መወሰን።

### ቁጥሮችና ግብረቶች በአስሮሽ ቤት

- የቦታ ዋጋ፦ ከ 100 በመለስ ደምር/ሪ
  - ሁለት-አሃዝ ቁጥር እና አንድ-አሃዝ ቁጥር መደመር፣
  - ባለሁለት-አሃዝ ቁጥር እና የ 10 ብዜት መደመር፤
  - የኮንክሪት ናሙናዎችን በመጠቀም ወይም ስዕሎችን እና በቦታ ዋጋ ስልቶችን መሠረት በማድረግ የስሌት ባህርያትን፣ እና/ወይም በመደመር እና በመቀነስ መካከል ያለውን ግንኙነት በመጠቀም፣
  - ስትራተጂዉን/ስልቱን ወደ ጽሑፍ ዘዴ ማዛመድ እና በጥቅም ላይ የዋሉ ምክንያቶቹን መዘርዘር፤
  - ባለሁለት አሃዝ ቁጥሮችን መደመር ማለት፣ የአስር ቤት እና አስር ቤትን፣ የአንድ ቤት እና የአንድ ቤትን መደመር፣ እና አንዳንድ ጊዜ አስር ቤትን ማጣመር አስፈላጊ ነው።
- የቦታ ዋጋ፦ ከ 10 - 90 ባለው ማእቀፍ ውስጥ የ10 ብዜትን ከ10 - 90 ማዕቀፍ ዉስጥ ካለ የ10 ብዜት መቀነስ፣
  - የኮንክሪት ናሙናዎችን በመጠቀም ወይም ስዕሎችን እና በቦታ ዋጋ ስልቶችን መሠረት በማድረግ የስሌት ባህርያትን፣ እና/ወይም በመደመር እና በመቀነስ መካከል ያለውን ግንኙነት በመጠቀም፣
  - ስትራተጂዉን/ስልቱን ወደ ጽሑፍ ዘዴ ማዛመድ እና በጥቅም ላይ የዋሉ ምክንያቶቹን አስረዳ(ጂ)።

### ግብረቶች እና የአልጀብራ አስተሳሰብ

- ከ20 ቁጥር በታች በሚከተሉት ስልቶች በመጠቀም መደመር እና መቀነስ
  - በመቁጠር፤
  - በዚህ መልክ አስር በማድረግ(ምሳሌ፣ 8 + 6 = 8 + 2 + 4 = 10 + 4 = 14)፤
  - ወደ ኣስር የሚመራ ቁጥርን መበተን (ለምሳሌ፦ 13 - 4 = 13 - 3 - 1 = 10 - 1 = 9)፤
  - በመደመር እና በመቀነስ መካከል ባለው ግንኙነት በመጠቀም (ለምሳሌ፣ 8+4= 12 እንደሚሆን በማወቅ፣ 12-8= 4) እንደሚሆንም ይታወቃል፤
  - ተመጣጣኝ ነገር ግን ቀላል ወይም የሚታወቅ ድምር መፍጠር (ለምሳሌ፦ 6 + 7 በመደመር የሚታወቀውን ተመጣጣኝ መፍጠር 6 + 6 + 1 = 12 + 1 = 13)።
- እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን በቅልጥፍና መደመር እና መቀነስ።
- በሁሉም ቦታዎች ያልታወቁ ያሉበት በ20 ውስጥ መደመርና መቀነስን በመጠቀም የማከል፣ የመቀነስ፣ ኣንድ ላይ ማሰባሰብ፣ መበተን፣ እና የማወዳደር ሁኔታዎችን የሚያካትቱ የቃል ፕሮብሌሞችን መፍታት።
- ለመደመር እና ለመቀነስ የሂሳብ ስሌት ባህርዮችን እንደስልት ተግባራዊ አድርግ/ጊ።
- መቀነስን እንዳልታወቀ-ተደማሪ ፕሮብሌም መገንዘብ።
- የእኩል ምልክትን ትርጉም መገንዘብ፣ እናም መደመርና መቀነስ የሚያካትቱ ቀመሮች ትክክል ወይም ስህተት መሆናቸውን መወሰን።
- ከሦስት ሙሉ ቁጥሮች ጋር በማገናኘት በመደመር ወይም በመቀነስ ቀመር ውስጥ ያልታወቀ ሙሉ ቁጥርን ለይ።

## ምንባብ

### የማንበብ ግንዛቤ፦ ስነ ፅሁፍ

- ቁልፍ ስለሆኑ ዝርዝሮች እየጠየቅህ(ሽ) መልስ ስጥ/ስጪ።
- በታሪኩ ወይም በግጥሙ ውስጥ ስሜት ገላጭ የሆኑ ወይም ስሜት የሚሰጡ ቃላት እና ሐረጎችን ለይ።
- በጽሑፉ ላይ በተለያዩ ነጥቦች ታሪኩን የሚናገረው ማን እንደሆነ ለይ።
- ከቅስቀሳና ድጋፍ ጋር፣ ለ1ኛ ክፍል ተገቢ ውስብስብነት ያለው ስድ ንባብና ግጥም ማንበብ።

### ምንባብ የመረዳት (የማወቅ) ችሎታ፦ መረጃዊ

- ከጽሑፍ ውስጥ ስለ ቁልፍ ዝርዝሮች ጥያቄዎችን ይጠይቁ እና ይመልሱ።
- የኣንድን ፅሁፍ ዋናውን ርእስ መለየት እና ቁልፍ ዝርዝሮችን መልሶ መንገር።
- በስነጽሑፍ ላይ ቁልፍ ማረጋገጫዎችን እና መረጃዎችን/ኢንፎርሜሽን ለማመልከት የተለያዩ የጽሑፍ ባህሪያት/ መለያዎችን (ለምሳሌ፦ አርእስት፣ ማውጫ፣ የቃላትና ፍቺዎቻቸው ዝርዝር፣ ኤሌክትሮኒክ ዝርዝሮች፣ልዩ ምልክቶች/ተምሳሌት) ማወቅና መጠቀም።
- በሥዕል የተደገፈ ማሳያ፣ ፎቶ/ሥዕል፣ እና በጽሑፍ የተሰጠ መረጃ/ኢንፎርሜሽን መካከል ልዩነቶችን መገንዘብ/ማሳየት።
- ጥያቄዎችን በመጠየቅና መልስ በመስጠት በጽሑፍ ውስት የሀረጎችን ትርጉም ግለጽ/ጪ።
- በአንድ ርእስ ላይ በተጻፉ ሁለት ጽሑፎች መካከል መሠረታዊ ተመሣሣይ ነገሮችን እና ልዩነቶችን (ለምሳሌ፦ በሥዕላዊ አገላለጽ፣ በማስረዳት፣ ወይም በቅደምተከተል) ለይ።
- ከቅስቀሳና ከድጋፍ ጋር፣ ለ1ኛ ክፍል በኣግባቡ ውስብስብ የሆነ መረጃያዊ ፅሁፍ ማንበብ።

### ቋንቋ፦ የቃላት እውቀት እና አጠቃቀም

- ዘለግ ባለ/በጎላ ድምፅ ከተነበበ ጽሑፍ ላይ ወይም በቃላት ወይም በሌላ ሚዲያ የቀረቡ መረጃዎችን በተመለከተ ቁልፍ ዝርዝሮችን ይጠይቁ እና ይመልሱ።
- ተጨማሪ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ወይም አንድ ያልገባህ(ሽ)ን ነገር የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ተናጋሪው(ዋ) ምን እንደሚል/እንደምትል ጠይቅ/ጠይቂ እና መልስ/መልሺ።
- ያልታወቁ ወይም በርካታ ትርጉም ያላቸውን ቃላት እና ሐረጎች፣ ለ1ኛ ክፍል ምንባብ ይዘት ከተደረደሩት ስልቶችን በመለዋወጥና በመምረጥ ትርጉማቸውን ማብራራት ወይም መወሰን።
- የፅንሰ ሃሳብ መረዳትን ለማሳየት ቃላትን በየፈርጁ መለየት።

### መሰረታዊ ክህሎቶች፦

- ስለ ህትመት፣ የንግግር ቃላት፣ መርሃ-ትምህርት/ፊደላት፣ እና ድምፆችን መዋቅራዊ እና መሠረታዊ ለየት ያለ ባህርይ መገንዘብህ(ሽ)ን በተግባር አሳይ።
- የቃላት ፍቺዎችን በማወቅ በክፍል-ደረጃ የሚመጥን የንግግር ድምፀት እና የቃላት ትንታኔ ችሎታ መተግበር።
- በአእምሮ የመያዝ ችሎታ/መረዳትን ለማገዝ በትክክል በብቃት እና በማቀላጠፍ ማንበብ።

## ጽሑፍ

### መረጃ የሚሰጥ/ትምህርታዊ/ገላጭ

- በአነስተኛ ቡድን ለውይይት አንድ ርእስ ላይ ጥያቄ ማንሳት።

- እነርሱ በሚያነሱት ርእስ ላይ ትምህርታዊ/የማብራሪያ ጽሑፍ መጻፍ፣ ስለ ርእሱ አንዳንድ ማስረጃ/እውነታ መስጠት፣ እና መደምደሚያ ሃሳብ መስጠት።

**ሂደት፣ ውጤት፣ ጥናት/ምርምር**

- በጋራ የሚካሄድ ጥናት ላይ መሳተፍ።
    - በአርዕስቱ ላይ ማተኮር፣ ከአቻዎች/እኩዮች ለሚነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች መመለስ፣ እና ተጨማሪ ማብራሪያዎችን በመስጠት እነደአስፈላጊነቱ ጽሑፍን ማጠናከር።
- ጽሑፍ ለማዘጋጀት እና ለማሳተም የተለያዩ ዲጅታል መገልገያዎችን መጠቀም፣ ከእኩያሞቹ ጋር መተባበርን ጨምሮ።
- ከልምድ/ገጠመኝ የተገኘ መረጃ በማስታወስ/በመጥቀስ ወይም ከተሰጡ ምንጮች መረጃ በመሰብሰብ ለጥያቄዎች መልስ መስጠት።

**የቋንቋ አጠቃቀም**

- ሰዎችን፣ ቦታዎችን፣ ግዑዝ እቃዎች፣ እና የተፈጸሙ ድርጊቶችን በዝርዝር አግባብ የሆኑ ሃሳቦችን እና ስሜትን በመግለጽ ማስረዳት።
- ስዕል ወይም ሌላ የሚታዩ ነገሮችን አስፈላጊ ከሆነ በመጨመር አመለካከቶችን፣ አስተሳሰቦችን፣ እና ስሜቶችን ማብራራት/መግለጽ።
- ለስራ እና ለትክክለኛ ሁኔታ አግባብነት ሲኖራቸዉ የተሟሉ ዐረፍተ ነገሮችን ማፍለቅ።
- በመሠረታዊ አረፍተ ነገሮች ይዘት ላይ (ለምሣሌ፦ እርሱ በአንድ እግር ይዘላል፣ እኛ በአንድ እግር እንዘላለን) የነጠላ እና የብዙ ቁጥር ስሞችን ከተስማሚ ግሦች ጋር ተጠቀም/ሚ።
- ያለፈውን፣ የአሁኑን፣ እና የወደፊቱን መንፈስ (ለምሳሌ፣ Yesterday/ትናንት ወደቤት ሄድኩኝ/walked፤Today/ዛሬ ወደ ቤት እሄዳለሁ/walk፤ Tomorrow/ነገ ወደ ቤት እሄዳለሁ/will walk) ለማስተላለፍ ግሶችን መጠቀም።
- በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ቅፅሎችን፣መስተጻምሮችን፣ መስተዋድዶችን ተጠቀም/ሚ።
- ለጥያቄዎች ለመመለስ ቀላል እና ጥቅል መግለጫዊ፣ ጥያቄያዊ፣ ግዴታ/ትዕዛዛዊ፣ እና የቃለአጋኖ ዓረፍተነገሮችን ፍጠር እና አስፋፋ/ፍጠሪ እና አስፋፊ።
- በመደበኛ የእንግሊዝኛ ትልቁን ፊደል መጠቀም፣ ስርአተ ነጥብ አገባብ/አጠቃቀም፣ እና የቃላት አፃፃፍ ችሎታ/ብቃት አሳይ።

***ትረካ***

- በርካታ ክውነቶችን ከዝርዝሮች ጋር የሚተርኩ ታሪኮችን ለመጻፍ የተለመዱ ተሞክሮዎችን ማስታወስ።
- በትረካ ውስጥ ክውነቶችን ተራ ማስያዝ።
- የመዝጊያ መልእክት ስጥ/ስጪ።
- ትርጉሙን ለማስተላለፍ ስእሎችን መጨመር።

**አስተያየት**

- ርእሱን የሚያስተዋውቁባቸው የአስተያየት ፅሁፎች መፃፍ ወይም የሚፅፉለትን መፅሃፍ ስም ማስታወቅ።
- ኣንድን ኣስተያየት ማስቀመጥና ለኣስተያየቱ ምክንያት መስጠት።
- የመዝጊያ መልእክት ስጥ/ስጪ።

## ሳይንስ

**ፊዚካል ሳይንስ**

- የተለያዩ ነገሮች ሊታዩ የሚችሉ ባህርያትን እና የተሰሩባቸውን ቁሳቁሶች፣ ከምርመራዎች በተገኘ መረጃ በመጠቀም፣ ማወዳደር።

**የመሬትና የህዋ/ጠፈር ሳይንስ**

- ተፈጥሮአዊ ባህሪዮችን የሚገልጹ/የሚያመላክቱ ቁሳቁሶችን/ነገሮችን ለይ የምድር-ገፅታ።
- በሰዎች የተፈጠሩ እና በሰው ያልተፈጠሩ አካባቢያዊ ገጽታዎችን መለየት።
- በተፈጥሮአዊ አካባቢ ያሉ ለውጦችን እና በምድር ገፅ ላይ የሚታዩ ለውጦችን ለይ።
- በአካባቢ የተፈጥሮአዊ እና ሰው-ሠራሽ ቁሳቁሶችን ባህርይ ግለጽ/ጪ እና አወዳድር/ሪ።

**የኢንጂነሪንግ ንድፍ እና ሂደት**

- የቴክኖሎጂን ባህርያትና ስፋት ግንዛቤ ማዳበር።
- በቴክኖሎጂ እድገትና አጠቃቀም የማህበረሰብን ሚና ግንዛቤ ማበልፀግ።
- ስለ ምህንድስና ንድፍ እውቀትን የበለጠ ማዳበር።
- የመላ ፍለጋ፣ ምርምርና እድገት፣ ፈጠራ፣ እና ሙከራ ማካሄድ ፕሮብሌም በመፍታት ረገድ ያላቸው ሚና ግንዛቤ ማዳበር።
- የንድፍ ሂደት ትግባሬ ችሎታዎችን ማዳበር።
- የውጤቶችንና የስርኣቶችን ተፅእኖ ለመገምገም ችሎታዎችን ማበልፀግ።

## ማህበራዊ ጥናቶች

**ጂዮግራፊ**

- ምድር ላይ ያሉ ቦታዎችን ለማግኘትና ለመግለፅ በጂዮግራፊካዊ መሳርያዎች መገልገል።
- ጂኦግራፊያዊ ባርያትን በመጠቀም የአካባቢ ቦታዎችን ግለጽ/ጪ።
- ሰዎች አካባቢያቸውን እንዴት እንደሚቀይሩት/እንደሚያሻሽሉት፣ እንደሚንከባከቡ፣እና እንዴት ከአካባቢያቸው ጋር እንደሚላመዱ አስረዳ/ጂ።

## መረጃዊ/ኢንፎርሜሽናል ማንበብ እና መጻፍ

- ተፈላጊ መረጃን ለማሟላት ጥያቄዎችን መፍጠርና ማሻሻል።
- በልቦለድ እና ልቦለድ-ባልሆነ እና በሃቀኛ ህይወት ውስጥ ግንኙነቶችን መለየት።
- ኣሃዞችን/መረጃዎችን በተለያዩ ቅርፀቶች መመዝገብ።
- ለማጋራት የሚያስፈልጉትን መረጃ ግኝቶች/ እና ድምዳሜ ለማዘጋጀት የተለያዩ ቅርፀቶችን ይጠቀሙ።

## ስነጥበብ

**የሥነጥበብ ፈጠራ እና ከሥነጥበብ ጋር ያለ ግንኙነት**

- ስለ ሥነጥበብ ሥራ በርካታ ሃሳቦችን ለማፍለቅ በአንክሮ አጢን/አጢኚ እና መርምር(ሪ)።
- ስለ ቦታ/ሥፍራ ሃሳቦችን ለመግለጽ የሥነጥበብን መሠረታዊ ነገር/ዋና ነገር/ባህርይ እና የንድፍ መርሆችን ተጠቀም/ሚ።
- የስነ ጥበብ መሳሪያዎችን፣ ሚዲያ፣ እና የስራ ቦታን ሲጠቀሙ ተገቢውን ሂደት ያሳዩ።
- የሥነ ጥበብ መሥሪያዎችን በዘዴ በመጠቀም የእደጥበብ ሥራ እውቀት አዳብር(ሪ)።
- ለቦታ ምላሽ የሥነ ጥበብ ሥራ ይፍጠሩ።
- በተለያዩ ቦታዎች ሰዎች ለምን የእደጥበብ ሥራ እንደሚሠሩ ምክንያቶችን ለይተህ(ሽ) ግለጽ(ጪ)።

**ስነጥበብን ማቅረብና ምላሽ መስጠት፡-**

- ለአውደ-ርዕይ በግል ከተሰበሰቡ የስነጥበብ ሥራዎች በመምረጥ ለምን እንደተመረጠ አስረዳ/ጂ።
- የተለያዩ ክፍት (ባዶ) ቦታዎች የስነጥበብ ሥራን እንዴት ሊያሻሽል እንደሚችል ለይ።
- ሙዚየም ላይ የሚገኝ የስነጥበብ ሥራ በሌሎች ቦታዎች ከሚገኝ ስነጥበብ ሥራዎች እንዴት በተለይ እንደሚታይ ምክንያቶችን ለይ።
- ተፈጥሯዊ፣ ሰው ሠራሽ፣ እና ምናባዊ አካባቢዎችን የውበት ባህርያትን በመገንዘብ አስረዳ/ጂ።
- የስነጥበብ ሥራዎችን ትርጉም ይዘት ለመተርጎም በፋይዳዊ ዝርዝር መድብ/ቢ።
- የስነጥበብ ሥራን በግል ለመገምገም ውጤታማነት የተመሠረተ መስፈርት ተግባራዊ አድርግ/ጊ።

## ሙዚቃ

**የሙዚቃ ንባብና ፅሁፍ/ቅኝት**

- የቀላል ምትና የድምፅ ቃና ቅርፀቶችን ማንበብ።
- የቀላል ዜማ እና የሙዚቃ ቃና ደርዝ/አወራረድን፣ የሙዚቃ ምልክት በቦታ እና በመስመር ላይ ጻፍ/ፊ።

**የሙዚቃ ፈጠራ**

- ዝማሬን ወይም ትረካን ለማሻሻል/ለማጉላት መሣሪያዎችን በመጠቀም በመድረክ ላይ ፈጥሮ መሥራት።
- ቀላል ምት/የዜማ አወራረድ እና ጣዕመ  ዜማዊ ቅጦችን መፍጥር እና ተምሳሌታዊ አቀራረብ/iconic representation በመጠቀም መቃኘት።

**የሙዚቃ ምላሽ/ዝንባሌ**

- በመማሪያ ክፍል ውስጥ ልዩ ልዩ መሣሪያዎችን በእይታ እና በድምፅ ለይ።
- ለሙዚቃ ቀላል የእንቅስቃሴ ቅጥ ፍጠር/ሪ።
- የሙዚቃ ጽንሰሃሳቦች እና አስተያየቶች በተለያዩ የስነጥበብ ቅርጾች የሚገለጹባቸውን መንገዶች ለይ።
- በሙዚቃ እና በሌሎች ዘርፎች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች መፈተሽ/ማጥናት።

**ሙዚቃ መጫወት፡-**

- ከተለያዩ ታሪካዊ ወቅቶች እና ከአለም ባህሎች፣ የተወሰኑ ከኣጠቃላይ የመማርያ ክፍል ጥናቶች ጋር የተያያዙትን ጨምሮ፣ ዘፈኖችን/መዝሙሮችን እና ዳንሶችን ማቅረብ።

## የአካል ማጠንከርያ ትምህርት

**ጤና-አራማጅ አካላዊ ብቃትና እንቅስቃሴ**

- በጤና-ነክ የአካል ብቃት ክፍሎችን ማሻሻያ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ እና መለየት፡- የጡንቻ ጥንካሬ፣ aerobic capacity/cardiorespiratory endurance, and flexibility።
- የአካላዊ እንቅስቃሴ ጠቀሜታዎችን መርምር/ሪ።
- እንቅስቃሴ የሌለውን ልብ ከልብ እንቅስቃሴ ጋር በማወዳደር የተለያዩ እንቅስቃሴዎች የልብ ምት መጠን ላይ ተፅእኖ እንደሚኖራቸው ግንዛቤ ውሰድ/ጂ።
- የጡንቻ ጥንካሬን እና የጡንቻ ቻይነትን የሚያዳብሩ እንቅስቃሴዎችን ተለማመድ/ጂ።
- ግላዊ የመተጣጠፍ እና የመዘርጋት ችሎታ ፈትሽ/ሺ።

**የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እና እሳቤዎች**

- የተለያዩ ዓይነት የመነሣት እና የማረፍ ብቃትን በተግባር አሳይ።
- ፈጠራዊ የእንቅስቃሴ ክሂሎቶችን ማዳበር።
- የሰውነትን ቅርጽ በመለዋወጥ፣በድጋፍ መሰረት ላይ የአካል ሚዛንን ጠብቅ/ቂ።
- ክብደትን ከእግር ወደ እጅ የማስተላለፍ ተግባርን ተለማመድ/ጂ።
- የተለያየ የመውደቅ/የመንከባለል ዓይነት እንቅስቃሴዎችን አሥስ/ሺ።

## የጤና ትምህርት

**አመጋገብና የአካል ብቃት NF**

- በምግብ እና በስሜት መካከል ያለውን ግንኙነት በተግባር አሳይ።
- በምግብ እና በጤንነት መካከል ያለውን ግንኙነት አስተውል/ይ።
- ምግቦች በተለያየ ዓይነት ፈርጅ እንደሚመደቡ ተገንዘብ/ቢ።

**የቤተሰብ ህይወት እና ሰብአዊ ፍትወተ ሥጋ/ወሲባዊነት (FLHS)**

- ስለቤተሰብህ/ሽ ልዩ የሆነ ነገር ምን እንደሆነ ግለጽ/ጪ።
- የእድገትን ሂደት ግለጽ/ጪ።